## *ይህን ያውቁ ኖሯል ?*

በሀገራችን በመካሄድ ላይ ካለው ዘርፈ ብዙ የልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ አንዱና ዋነኛው የግብርና ልማት ዘርፍ ነው፡፡ በዚህ ዘርፍ በአሁኑ ወቅት ወሳኝ ሚና የሚጫወተው አርሶ አደሩ ነው፡፡ ይሁንና አርሶ አደሩ ወሳኝ ሚና በሚጫወትበት በአሁኑ ወቅትም ቢሆን የግል ባለሀብቶች በግብርና ልማት ሥራ ላይ መሳተፋቸው ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል፡፡ የግብርና ልማታችን እየተፋጠነ ሲሄድ የግል ባለብቶች ሚናም በዚያው መጠን እየጨመረ ይሄዳል፡፡ በአገራችንም የተሳካና ፈጣን የግብርና ልማት ከተካሄደ በሂደት የአርሶ አደሩ ሚና በግል ባለሀብቶች እየተተካ እንደሚሄድ አያጠራጥርም፡፡ ይህ ሂደት የማይቀር የተሳካ የገጠር ልማት ወጤት የሚያስገኝ ብቻ ሳይሆን ቀጣይነት ያለው እድገት ለማረጋገጥም አማራጭ የሌለው ሂደት ነው፡፡

የግል ባለሀብቶች በግብርና ልማት ዘርፍ በሁለት አጠቃላይ አቅጣጫዎች ሊሳተፍ ይችላሉ፡፡ አንደኛው አቅጣጫ ሰፋፊ ያልታረሰ መሬት ባላቸው አካባቢዎች ሰፋፊ ዘመናዊ እርሻዎችን በማቋቋም ሲሆን ይህ የግብርና ኢንቨስትመንት ከፍተኛ የገንዘብ ወጭና ትልቅ የካፒታል አቅም የሚጠይቅ ነው፡፡ ሌላው አማራጭ በውሱን መሬት ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ምርቶችን ማምረት ነው፡፡ ይህ አይነቱ የልማት ሥራ ከፍተኛ የካፒታል አቅም የሚጠይቅ አይደለም ከዚህ ይልቅ የግብርና ሞያ ብቃትና ገበያዎችን ሰብሮ የመግባት ችሎታ ይጠይቃል፡፡ የአገር ውስጥ ባለሀብቶች በነዚህ መስኮች እንዲሳተፉ መርዳትና ማበረታታት የግል ኢንቨስትመንት ከማጠናከር አኳያ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

ከዚህ አጠቃላይ የፖሊሲ ማዕቀፍ በመነሳት አጠቃላይ የአገራችን የመሬት ይዞታና ለውጭ ባለሀብቶች የተሰጠውን መሬት መጠን ለግንዛቤ እንዲረዳ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- አገራችን 74.3 ሚሊዮን ሄክታር ለእርሻ ተስማሚ የሆነ መሬት አላት፡፡
- ከዚህ ውስጥ 15.4 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በአነስተኛ ባለሀብቶችና በገበሬዎች እየለማ የሚገኝ መሬት ነው፡፡
- ከላይ በተገለፀው መሠረት የግል ባለሀብቱን ተሳትፎ ለማጐልበት ሲባል በቅርቡ የክልልና የፌዴራል መንግሥታት በጋራ በቆላማ የአገራችን አከባቢዎች ጥቅም ላይ ያልዋለ 1.73 ሚሊዮን ሄክታር ለሰፋፊ መካናይዝድ እርሻ ልማት የሚውል መሬት ለይተዋል፡፡
- በጋራ ከተለየውም 1.73 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ውስጥ እስካሁን ድረስ 363000 ሄክታር መሬት ለተለያዮ የውጭ ባለሀብቶች ተሰጥቷል፡፡
- የውጭ ባለሀብቶቹ ከተለያዩ አገሮች የመጡ ሲሆን ከነዚህም መካከል ከህንድ፣ ከኢራን፣ ከሳውዲአረቢያ፣ ከየመን፣ ከጂቡቲ፣ ከፖኪስታን፣ ከጀርመን፣ ከናይጄሪያ ከብራዚልና ከእስራኤል የመጡ ይገኙባቸዋል፡፡
- ባለሀብቶች የእርሻ መሬቱን በሊዝ ስምምነት የወሰድ ሲሆን በክልል ደረጃ ስርጭቱ ስንመለከተው በደቡብ ክልል 115925 ሄክታር፣ በኦሮሚያ ክልል 91892 ሄክታር፣ በቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል 6500 ሄክታር፣ በአፋር 1600 ሄክታር፣ በሶማሌ ክልል 49000 ሄክታር እንዲሁም በጋምቤላ 147000 ሄክታር መሬት ነው፡፡

ይኸው ታላላቅ ባለሀብቶች በእርሻ የኢንቨስትመንት መስክ ላይ እንዲሳተፉ የሚያስችለወ ብሩህ ፓሊሲ ከሀገሪቱ አርሶ አደሮች ምትክ የለሽ ጥረት ጋር ተዳምሮ የገጠሪቱን ኢትዮጵያና እንዲያም ሲል የሀገራችንን የኢኮኖሚ ደንደስ በማጐልበት በአጭር ጊዜ ውስጥ ድህነትን ለመርታት ለምናደርገው ግብግብ አንድ ተጨማሪ የፍልሚያ መድረክ ነው፡፡

ታዲያስ ወገን ከዚህ አንፃር የእርሶ ሚና ምን ይሁን ? መረጃ በመስጠት፣ በካፒታል አቅም ካላቸው ወገኖች ጋር በሽርክና ኢንቨስት በማድረግ ወይም የጋራ ሕብረት መስርቶ መሳተፍ ወሳኝ በመሆኑ ርብርብ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

*የአገሩን በሬ በአገሩ ሰርዶ ይባል የለ !!*